# ይናገራል ፎቶ የግንቦቱ መሪ






ይናገራል ፎቶ - ከቃላት አብልጦ
የሰውን ገመና - ሚስጥሩን ገላልጦ
አድርባይ ስግብግብ - ለሆዱ ያደረ
ተጎናባሽ ሆኖ - እድሜ ልክ የኖረ
ብርሀኑ ነጋን - ዛሬ ቀን ጥሎታል
ከሀዲ መሆኑን - ቀባጥሮ አሳይቷል
እኛስ ስንጮህ ነበር - በየ አጋጣሚው
ህዝቡን ሲያዘናጋ - ግራ ሲያጋባው
ቡራዩ ሲታረድ - አፉን የለጎመ
ጣፎ ሲፈናቀል - ከጎኑ ያልቆመ
ጌዲዮ ሲቸገር - ገፍ ያላወገዘ
በአዲስ አበቤዎች - ሲቀልድ ተያዘ
የኢትዮጵያዊ ኪስ - ሲያሟጥጥ የኖረ
የአማራ ልጆችን - ደመከልብ ያስቀረ
የግንቦቴን ጥፋት - ጊዜ መሰከረ
በአዲስ አበባ አቋም - ሲተች ሲደነፋ
አይወድቁ ወደቀ - ባፍጢሙ ተደፋ
ተስፋ በጣሉበት - ጓዶቹ ተተፋ
ያለቦታው ገብቶ - ያለሰገባው
ብሬ በድፍረቱ - ገደል የገባው
ህሊናውን ሽጦ - አገር አወቀው
እንደ እስክንድር አይነት . ወገኑን አክባሪ
ትልቅ ስብእና - ለአገር ተቆርቋሪ
ብሬ ሲጎነትል - ሊያገኝ ፍርፋሪ
ሲንኮታቶት ታየ - የግንቦቱ መሪ

ዘውዲቱ የማነ

2019-03-28